ፓርላማ ዜና መጽሔት

7ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ1ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ በጥቅምት 2019 ዓ.ም በአካሂዳቸው መደበኛ ስብሰባዎች በኢፌዲሪ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል ለኃይል ሴክተር ሪፎርም ኢንቨስትመንትና ማዘመኛ ምዕራፍ አንድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል የ145.8 SDR ወይም 200 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አፅድቋል።

በተያያዘ ምክር ቤቱ የምክር ቤቱን ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ አባላት፣ የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን፣ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ዕጩ አመራር እና አባላት ምደባ አስመልክቶ የቀረበውን የወሳኔ ሀሳብ መርምሮ አጽድቋል፡፡

የጥቅምት ወር ዜና መጽሔታችን እነዚህንና ሌሎችን አበይት ምክር ቤታዊ ጉዳዮች ታስነብባለች፡፡

ዓበይት ርዕሶች

•ሕግ አወጣጥ

መልካም ንባብ!
ጥቅምት፣ 2019 ዓ.ም

19ኛው ብሔራዊ የሠንደቅ ዓላማ ቀን “ሠንደቅ ዓላማችን ለብሔራዊ መግባባትና ለአንድነታችን” በሚል መሪ ቃል በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት 2 ቀን 2019 ዓ.ም ተከብሯል።



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አህመድ ሽዴ በበኩላቸው፣ ሰንደቅ ዓላማችን የኢትዮጵያ የጋራ ታሪክ የተጻፈበት፣ የጽናትና የጀግንነት ምልክት መሆኑን ነው የገለጹት።

የተከበሩ አቶ አህመድ በንግግራቸው የብሔራዊ ሠንደቅ ዓላማ ቀን መከበር ለሀገራችን ብሔራዊ መግባባትና ለአንድነት መጠናከር እጅግ ወሳኝ መሆኑን ጠቁመው ሠንደቅ ዓላማችን ሀገራዊና ወቅታዊነቱን በጠበቀ መልኩ የሚከበረው ለብሔራዊ መግባባትና ለአንድነት ግንባታ ትልቅ ፋይዳ ስላለው ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያውያን የጋራ ታሪክ በደማቅ ሁኔታ የተፃፈበት ድንቅ የታሪክ መሠረት መሆኑን ገልጸው ሠንደቅ ዓላማችን የሕዝባችንን የፅናትና የጀግንነት ታሪክ የሚመሰክር እንዲሁም የነጻነታችን እና የሉዓላዊነታችን ገጽታ ሆኖ የሚያገለግል የክብር መገለጫችን ነው ሲሉ የተከበሩ አቶ አህመድ ተናግረዋል።

የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕግ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሠረት ይህንን ብሔራዊ የሠንደቅ ዓላማ በዓልን በበላይነት የማስተባበር፣ የመምራት እና የሰንደቅ ዓላማችንን ክብር የሚያደምቁ ሁኔታዎችን የማስተካከል ሰፊ ኃላፊነት የተጣለበት መሆኑን ገልጸው ይህ ኃላፊነት የታሪክ፣ የሕግና የሕዝብ አደራ በመሆኑ ምክር ቤቱ በከፍተኛ ቁርጠኝነትና ትጋት ስራውን እየተወጣ እንደሚገኝም አፈ ጉባኤው አስገንዝበዋል።






አርበኞች አባቶቻችንና እናቶቻችን ደምና አጥንታቸውን ከስክሰው ያስረከቡንን ሠንደቅ ዓላማ በክብርና በልዕልና ጠብቆ ማቆየት የትውልዱ አደራ ነው ሲሉ ፕሬዝዳንት ታዬ አጽቀሥላሴ ገልጸዋል።

የዘንድሮ የብሔራዊ ሠንደቅ ዓላማ ቀን አከባበር ሀገራችን ኢትዮጵያ አጠቃላይ ሀገራዊ ምርጫን በስኬት አጠናቅቃ አዲስ የሕዝብ አደራ የተቀበለ መንግሥት በወጠነችበት ማግስት መከበሩ ልዩ እንደሚያደርገው የገለጹት ፕሬዝዳንት ታዬ የሕዝብ አደራ የተቀበሉት የምክር ቤት አባላትም የሠንደቅ ዓላማችንን ክብርና ልዕልና የሚመጥን ሀገራዊ አገልግሎት የመስጠት ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነት እንዳለባቸው አክለው ገልጸዋል።

ሀገራችን በየዘመናቱ የሚገጥሟትን ፈተናዎች ማሸነፍ የምትችለው የብዝኃነት ውበቷን አክብራ በብሔራዊ መግባባትና በጽኑ አንድነት ስትቆም መሆኑን ጠቁመው፤ የሕግ የበላይነትን በማስከበር፣ የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን በማፋጠን እንዲሁም በምግብ ራስን ለመቻል የተጀመሩ ታላላቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን ዳር በማድረስ ሀገራዊ እድገትን ማረጋገጥ ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በዕለቱ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ክቡር ቴዎድሮስ ምህረት አማካኝነት የሠንደቅ ዓላማ ቃለ-መሃላ የማስፈጸም ሥነ-ሥርዓት ተከናውኗል።






7ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ1ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ጥቅምት 3 ቀን 2019 ዓ.ም በአካሄደው 2ኛ መደበኛ ስብሰባ በኢፌዲሪ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል ለኃይል ሴክተር ሪፎርም ኢንቨስትመንትና ማዘመኛ ምዕራፍ አንድ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል የ145.8 SDR ወይም ወይም 200 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ አፅድቋል።






የብድሩ ዓላማ የአዲስ አበባን የኃይል ማስተላለፊያ መረብ ለማጠናከር፣ አዳዲስ የኃይል ጣቢያዎችን መገንባትና ነባሮቹን ማሻሻል እንዲሁም የመሬት ውስጥ የኃይል ማስተላለፊያ መስመሮችን መዘርጋት የሚያስችል መሆኑን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የተከበሩ አቶ ፍቃዱ ተሰማ ለምክር ቤቱ በአቀረቡት ማብራሪያ ገልጸዋል።

አክለውም ኢትዮጵያ ለምታስተናግደው ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ (COP 32) አስተማማኝና ዘመናዊ የኃይል አቅርቦትን ለማረጋገጥ የብድር ስምምነቱ ሚናው የጎላ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ብድሩ ቀላልና ስምምነቱ የ6 ዓመት የእፎይታ ጊዜን ጨምሮ በ 31 ዓመታት ውስጥ ተከፍሎ የሚጠናቀቅ መሆኑን የገለጹት የተከበሩ አቶ ፍቃዱ ከሀገሪቱ የብድር አሰጣጥና አስተዳደር ስትራቴጂ ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጣጣምና ለዘላቂ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው መሆኑን ለምክር ቤቱ አስገንዝበዋል።



ምክር ቤቱ በኢፌዲሪ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል ለኃይል ዘርፍ ማሻሻያ፣ ኢንቨስትመንትና ማዘመኛ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የተፈረመውን የ145.8 SDR ወይም 200 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ተጨማሪ ቀላል የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅን፤ አዋጅ ቁጥር 1441/2019 አድርጎ በሙሉ ድምፅ አጽድቆታል።

7ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ አመት የሥራ ዘመን ጥቅምት 5 ቀን 2019 ዓ.ም በአካሄደው 3ኛ መደበኛ ጉባኤው የምክር ቤቱን ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ አባላት፣ የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት፣ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ዕጩ አመራር እና አባላት ምደባ አስመልክቶ የቀረበውን የወሳኔ ሀሳብ መርምሮ አጽድቋል፤





የተከበሩ አፈ ጉባኤ አቶ አሕመድ ሽዴ እጩ አማካሪዎችን ለምክር ቤቱ ባቀረቡበት ወቅት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/19 መሠረትም ለምክር ቤቱ የሚያስፈልጉ ቋሚ እና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ማዋቀር እንደሚገባ በሕግ መደነገጉን ገልጸዋል።

እንዲሁም በምክር ቤቱ የአሠራር እና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008 አንቀጽ 152 መሠረት ምክር ቤቱ ሲመሠረት ከሚቋቋሙት ኮሚቴዎች መካከል የምክር ቤቱን አጀንዳ የሚያዘጋጅ፣ ዓመታዊ በጀት የሚያቀርብ፣ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስ እና የንብረት አስተዳደርን የሚከታተል እና የሚቆጣጠር እንዲሁም የምክር ቤቱን ደንብ የሚተረጉም እና አፈጻጸሙን የሚያግዙ መመሪያዎችን የሚያወጣ አማካሪ ኮሚቴ ይገኝበታል።

ኮሚቴው በዚሁ ደንብ አንቀጽ 152/1 መሠረት የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤ እና የፓርቲ ተጠሪዎችን ጨምሮ የፓርላማ ቡድኖች ባላቸው የመቀመጫ መጠን የሚወከሉበት እና በአፈ ጉባኤው የሚመራ መሆኑ ይታወቃል።

የተከበሩ አፈ ጉባኤ አቶ አህመድ ሽዴ ባቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ፣ በእጩዎች አመራረጥ ወቅት ከመንግሥት ተጠሪ እና ከፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ጋር ሰፊ ውይይት መደረጉን ገልፀው፣ አሠራሩም ብዝኃነትን፣ ብቃትን፣ የሥራ ልምድን፣ በምክር ቤቱ መቀመጫ ያላቸውን የተፎካካሪ ፓርቲዎች ውክልና፣ እንዲሁም የአዳዲስ እና የነባር አባላትን ጥምረት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን አስረድተዋል።

በዚህም መሠረት የኮሚቴው አባላት፡-

1. የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ
2. የምክር ቤቱ ምክትል አፈ ጉባኤ
3. በምክር ቤቱ የመንግሥት ዋና ተጠሪ
4. በምክር ቤቱ ሁለት ረዳት የመንግሥት ተጠሪዎች
5. የተከበሩ ዶክተር አሸብር ወልደ ጊዮርጊስ
6. የተከበሩ አቶ አብዱ ሐሰን
7. የተከበሩ ዶ/ር ጥላሁን አርዱኖ
8. የተከበሩ ዶ/ር ካሳሁን ደለነ

9. የተከበሩ አቶ የሱፍ ኢብራሂም
10. የተከበሩ አቶ ዝኑር አብዱልዋሂብ
11. የተከበሩ ወ/ሮ ፈተና ባዩ
12. የተከበሩ አቶ ለገሰ ላንቃሞ

ምክር ቤቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55/19 እና በደንብ ቁጥር 6/2008 አንቀጽ 152 መሠረት የቀረበውን የምክር ቤቱ ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ አባላት የመሰየም ውሳኔ ሀሳብ ቁጥር 2/2019 አድርጎ በሙሉ ድምፅ አጽድቋል፡፡



ምክር ቤት የቋሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ አጽድቋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴዎች ተግባር እና ኃላፊነት በአዲስ ማደራጀት ያስፈለገው ስያሜያቸው የተቀየሩ ተቋማት ስላሉ እና የመደመር መንግሥትን ዋና ስትራቴጂ እቅድ መሠረት ያደረገ እንደሆነ የተከበሩ አፈ-ጉባኤ አህመድ ሽዴ ገልፀዋል፡፡

የምክር ቤት አባላቱ አንዳንድ የፌዴራል መንግሥት ተቋማት እንደየሥራባህሪያቸው በእያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ መካተት እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

በዚህ መሠረት ምክር ቤቱ የሚከተሉት አስራ ሶስት ቋሚ ኮሚቴዎችን አደረጃጀት አፅድቋል፡፡

1. የሕግ እና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
2. የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
3. የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
4. የሰው ኃብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
5. የጤና፣ ማህበራዊ ልማት እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
6. የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
7. የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
8. የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
9. የከተማ መሠረት ልማት እና ሎጂስቲክስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
10. የንግድ፣ ባህልና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
11. የብሔራዊ ስትራቴጂ፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
12. የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና
13. የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ናቸው፡፡

ለእያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ የሚኖሩት ሲሆን ሰብሳቢዎቹ በአፈጉ ባኤው አቅራቢነት በምክር ቤቱ ተመርጠዋል፡፡

ምክር ቤቱ ቋሚ የኮሚቴዎች አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን የቀረበ የውሳኔ ሃሳብ፤ ውሳኔ ሃሳብ ቁጥር 3/2019 አድርጎ በሙሉ ድምፅ አፅድቋል፡፡

በዚሁ ዕለት ምክር ቤቱ የቋሚ ኮሚቴዎች ዕጩ አመራርና አባላትን ምደባ አስመልክቶ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ አፅድቋል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አቶ አህመድ ሽዴ ባቀረቡት የውሳኔ ሀሳብ በእጩዎች የአመራረጥ ሂደት ከምክር ቤቱ የመንግሥት ተጠሪ እና ከፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ጋር ሰፊ ውይይት የተደረገበት መሆኑን ገልፀው ብዝሓነትን፣ ብቃትን፣ የሥራ ልምድን፣ በምክር ቤቱ መቀመጫ ያላቸውን የተፎካካሪ ፓርቲዎችን ታሳቢ ያደረገ እንዲሁም አዲስ እና ነባር አባላትን ያካተተ ለማድረግ ጥረት መደረጉን አንስተዋል።

በዚህም መሰረት፡-
•የተከበሩ ቀነአ ያደታ (ዶ/ር)፡- የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ አቶ ታርጀት ደቦል፡- የሕግና ፍትህ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ አቶ መለሰ መና፡- የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ እሱባለው መብራት (ዶ/ር)፡- የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግሥቱ፡- የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ አቶ ጫላ ለሚ፡- የዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ አቶ ሰለሞን ላሌ፡- የንግድ፣ ባህልና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ አቶ ጣሂር መሀመድ፡- የንግድ፣ ባህልና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ የተከበሩ አቶ ደሳለኝ ወዳጄ፡- የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ

•የተከበሩ ወ/ሮ ወላይቴ ቢቶ፡- የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ ወ/ሮ ወሰነች ቶማስ፡- የብሔራዊ ስትራቴጂ፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ ወ/ሮ ዝናሽ ፀጋዬ ፡- የብሔራዊ ስትራቴጂ፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ ዲማ ኖጎ (ዶ/ር)፡- የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ ፊትሒ ማሕዲ (ዶ/ር)፡- የውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ ወ/ሮ የሺሀሳብ ፀጋው፡- የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ እሸቱ ተመስገን (ዶ/ር)፡- የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ አቶ አለማየሁ እጅጉ፡- የከተማ መሠረተ ልማት እና ሎጂስቲክስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ አወቀ አምዛዬ (ዶ/ር)፡- የከተማ መሠረተ ልማት እና ሎጂስቲክስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ አብርሃም አለማየሁ (ዶ/ር)፡- የመንግሥት ወጪ፣ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ ወ/ሮ አራሬ ሞሲሳ፡- የመንግሥት ወጪ፣ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ አቶ ንጋቱ ወልዴ፡- የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ ወ/ሮ ነፊሳ አልማህዲ፡- የውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ
•የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ፡- የጤና፣ ማህበራዊ ልማት እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ ወ/ሮ ጀሚላ ሲምቢሮ፡- የጤና፣ ማህበራዊ ልማት እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ

•የተከበሩ ነገሪ ሌንጮ (ዶ/ር)፡- የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ
•የተከበሩ ወ/ሮ ዘሃራ ሰምሬ፡- የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ሆነው ተሰይመዋል።

ምክር ቤቱ የቋሚ ኮሚቴዎች ዕጩ አመራርና አባላትን ምደባ አስመልክቶ የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ፣ ውሳኔ ሀሳብ ቁጥር 4/2019 አድርጎ በሙሉ ድምፅ አፅድቆታል።



ለበለጠ መረጃና አስተያየት
አድራሻ (Address)
ስልክ Tel:- 011-154-52-33
ነፃ ስልክ ጥሪ Free call 8557
ፖስታ ሳጥን ቁጥር P.O.Box : 80001
ኢ.ሜይል E-mail info@hopr.gov.et
በኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የኮሙኒኬሽን፣ አስተህምሮና ሙዚየም መሪ ሥራ አስፈፃሚ የተዘጋጀ፣